የሰበር መዝገብ ቁጥር 141527

ሕዳር 28 ቀን 2010 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

**አመልካች፡-** አቶ እለፋቸው ታምሩ    አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ እመቤት ተሾመ    አልቀረቡም

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል አስመልክቶ የቀረበን አፈጻጸም የሚመለከት ነው፡፡ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ሲደረግ የነበረውን የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተመለከተ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት አፈጻጸሙን ለመራው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ የይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት በላከው ምላሽ ቤቱን በዓይነት ለማካፈል የሚችል መሆኑን ገልጾ ክፍፍሉ ሲፈጸም ለግራቀኙ በደረሰው ንብረት የሐብት ማጋደል ስለሚኖርበት ግራቀኙ ልዩነቱን በማካካስ የሚፈጽሙት ነገር ካለ ሐሳባቸውን እንዲገልጹ መጥሪያ የተላከላቸው ቢሆንም የፍርድ ባለመብት ሃሳባቸውን ይዘው ቀርበው የፍርድ ባለእዳ ሀሳባቸውን ያላቀረቡ በመሆኑ አፈጻጸሙ በምን መንገድ መቀጠል እንዳለበት ፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲሰጥበት በማለት ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራቀኙ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ካደረገ በኋላ በዋናው ውሳኔ ላይ የግራቀኙ የጋራ ንብረት ናቸው በማለት ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ግራቀኙ ከተቻለ በዓይነት እንዲካፈሉት፤በዓይነት መካፈል ካልተቻለ ክፍፍሉን በተመለከተ በውሳኔው ላይ በተቀመጠው አማራጭ መሠረት እንዲካፈሉት በማለት የተሰጠ ውሳኔ ነው፤በፍርድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ቤቶቹ እኩል መካፈል እንደማይችሉ ተገልጿል፤የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ግራቀኙ እንዲካፈሉ ለማድረግ የግራቀኙን ሥምምነት ይጠይቃል፤ግራቀኙ በሰጡት አስተያየት ሥምምነት የሌላቸው መሆኑን የገለጹ በመሆኑ የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት በውሳኔው ላይ በቀጣይ በተቀመጡት አማራጮች መሠረት ውሳኔውን እንዲያስፈጽም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍ/ቤት አፈጻጸሙ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት እንዲፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ፍርዱ እንዳይፈጸም እና ዋጋ አልባ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፤የሚመለከተው አካል ፍርድ ያረፈባቸው ቤቶች ከዋናው ቤት ተነጥለው መሸጥ እንደማይችሉ፤ይዞታው ለሁለት እኩል ሲካፈል ለግራቀኙ ከ150 ካ.ሜ ያነሰ ቦታ ሊደርሳቸው ስለማይችል በዓይነት እኩል ማካፈል እንደማይቻል ያረጋገጠ በመሆኑ በፍርዱ በተቀመጡት ሌሎች አማራጮች መሠረት ፍርዱ ሊፈጸም አይችልም፤ፍ/ቤቱ ፍርዱን ለማስፈጸም ተስማሚ ነው የሚለውን ትዕዛዝ በመስጠት ፍርዱን ማስፈጸም ስላለበት ጉዳዩን በአግባቡ ካጣራ በኋላ ቤቶቹ የየራሣቸው የሆኑ ሁለት መግቢያ እና መውጫ በሮች ስኗኗቸው ግራቀኙ በፐሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ተካፍለው እንዲገለገሉባቸው ከማድረግ ውጪ ፍርዱ የሚፈጸምበት ሌላ አማራጭ ስለሌለ በፐሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት ተደጋጋሚ ትዕዛዝ ሲሰጥ ከቆየ በኋላ በሌላ አማራጭ መሠረት ፍርዱ ይፈጸም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የበታች ፍ/ቤቶች አከራካሪ የሆነው ቤት ሊካፈልም ሆነ ሊሸጥ የማይችል ነው፤ሊካፈል የሚችለው በተነጻጻሪ ካርታ ነው በማለት ባለሙያ አስተያየት በሰጠበት ሁኔታ በሌላ አማራጭ ይፈጸም በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 91(1)እና(2) እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሐብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሐብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል፤እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል በማለት ይደነግጋል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች የሐብት ማጋደል ባለበት ሁኔታ ቤቱን

በዓይነት ለማካፈል የግራቀኙ ሥምምነት ያስፈልጋል፤ግራቀኙ ስምምነታቸውን ባልሰጡበት ሁኔታ በዓይነት ማካፈል የማይቻል በመሆኑ በውሳኔው በቀጣይ በተቀመጠው የክፍፍል አማራጭ መሠረት ውሳኔው ሊፈጸም ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሱ ቢሆንም የሚመለከተው አካል ቦታው በዓይነት ሲካፈል እያንዳንዳቸው 150 ካ.ሜ ማግኘት አለባቸው ሁለቱም ሠዎች የየራሣቸው መግቢያ እና መውጫ መንገድ ስላላቸው ሰዎቹ የሚሥማሙ ከሆነ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መገልገል የሚችሉ መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ የአመልካች አቤቱታ ተጠሪ መጠለያ እና ቀለብ ለመንፈግ የቀረበ ነው ከማለት በቀር ክፍፍሉ በተነጻጻሪ ካርታ ቢፈጸም የሚያመጣባቸው ጉዳት መኖሩን በመግለጽ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / መከፋፈል እንሚችሉ በሚመለከተው አካል እስከተገለጸ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍል በተቻለ መጠን ባልና ሚስት ንብረታቸውን በዓይነት የመካፈል መብታቸውን ባስጠበቀ መንገድ ሊፈጸም ይገባዋል የሚለውን የክፍፍል መርህ ባስጠበቀ መልኩ በዚሁ ቤቶቹ በፕሮፖርሽን / በተነጻጻሪ ካርታ / እንዲከፋፈሉ በዚሁ አግባብ ክፍፍሉ ሲደረግ የበለጠ ይዞታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን ግምቱን እንዲከፍል በማድረግ ማስፈጸም ሲገባው በፍርዱ በተቀመጠው ሌላ አማራጭ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም በማለት መወሰኑ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 117839 ሕዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 193470 ሚያዝያ 18 ቀን 2009 የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ በፍርድ ሐተታው በተገለጸው መሠረት አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

-የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ.ቁ 117839 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡

-መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ